| 3ኛ ዓመት ቁጥር 1<br>3th Year No. 1 | ሐረር ሐምሌ 27 ቀን 1990<br>Harar August 3/1998 |
| --- | --- |

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ
# HARAR NEGARI GAZETA
## HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| ያንዱ ዋጋ 1:00 | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |
| --- | --- | --- |



ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 7/1990

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 7/1990------------------- ገጽ 34


## በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 7/1990 ዓ.ም

የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ለከተማው ነዋሪ ሕዝብ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደህንነትና ብልጽግና ለማስገኘትና ወደ ተሻለ የኑሮ ደረጃና እድገት ለማራመድ ከፍተኛ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በመረዳት

የማዘጋጃ ቤቱን የገቢ ምንጭ በማስፋፋት፣ ድርጅታዊ ብቃቱንና አስተዳደሩንም በማሻሻል የከተማው እድገት በዕቅድ እንዲመራ ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በማዘጋጃ ቤቱና በሥራና ከተማ ልማት ቢሮ እንዲሁም በቀበሌዎች መካከል ሊኖር የሚችለውን የሥራ ግንኙነት በአዲስ መልክ መደንገግ በማስፈለጉ፣

በአዲሱ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ መሠረት የከተማ ቦታን የኢንቨስት-መንት በሚያመች መልኩ ማስ ተዳደር አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት፣

በሐረሪ ሕዝብ ክልል ህገ-መንግሥት አንቀፅ 26/2/ሀ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 7/1990 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

1. «ህገ-መንግሥት» ማለት የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ህገ-መንግሥት ነው።
2. «ምክር ቤት» ማለት የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ነው።
3. «ቢሮ» ማለት የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ማለት ነው።
4. «ማዘጋጃ ቤት» ማለት የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ነው።
5. «የከተማ ሹም» ማለት የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤትን በበላይ ኃላፊነት እንዲመራ በክልሉ መንግሥት የሚሾም ባለሥልጣን ነው።
6. «ካዳስተር» ማለት በከተማ ክልል ለግብር አተማመን በመሬት ይዞታ ላይ የሚደረግ የዋጋ የመጠንና የባለቤትነት ይፋዊ ምዝገባ ወይም ጥናት ነው።
7. «ጠፍ እንስሳ» ወይም «ንብረት» ማለት ባለቤት የሌለው እንስሳ ወይም ንብረት ወይም ባለቤት እያለው ስድ ሆኖ ማዘጋጃ ቤቱ በሚሰይማቸው የህዝብ መገልገያ ስፍራዎች ላይ የተለቀቀ እንስሳ ነው።
8. «የሥነ-ሥርዓት አስከባሪ» /ተቆጣጣሪ/ ማለት ማዘጋጃ ቤቱ ለሕዝብ አገልግሎት እንዲሰጡ በሰየማቸው የከተማ ቦታዎች ላይ የጽዳት ጉድለት ባልተፈቀደ ቦታ የንግድ እንቅስቃሴ በሚያከናውኑ፤ ህገ-ወጥ ግንባታ በሚያከናውኑ ወዘተ . . . ተከታትሎ እርምጃ የሚያስወስድ አካል ነው።

### 3. የአዋጁ ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ ተፈጻሚ የሚሆነው በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሐረር ከተማ ላይ ብቻ ይሆናል።

### 4. ሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት የራሱ አርማ ይኖረዋል።

/ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።/

8. በተጨማሪም ከቢሮው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤

## ምዕራፍ ሶስት

### 8. ማዘጋጃ ቤቱ የቀበሌ መስተዳደሮችን በመከተል ስለሚኖረው ሥልጣንና ተግባር

የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት የቀበሌ መስተዳደሮችን በተመለከተ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

1. ቀበሌዎች ከቤት ኪራይና ከልማት ተቋማት የሚሰበስቡትን ገቢ በተከፈተላቸው የባንክ አካውንት ገቢ ማድረጋቸውን ያረጋግጣል፤ የሂሳብ አያያዝና አጠቃቀማቸውንም ይቆጣጠራል፤ እንደሁኔታውም መመሪያ ይሰጣል።

2. የቀበሌዎችን የሥራ ዕቅድና በጀት ገምግሞ ያጸድቃል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

3. የቀበሌዎች ገቢ የሚጠናከርበትን ዘዴ ይቀይሳል በሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ሲጸድቅም ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

4. የቀበሌ መስተዳደሮች ከልዩ ልዩ አገልግሎት ከሚሰበሰቡትና ለማዘጋጃ ቤቱ ፈሰስ ከሚደረጉት ገንዘብ እንደ አስፈላጊነቱ እየታየ ለቀበሌዎች ድጎማ ያደርጋል፤

5. የቀበሌ መስተዳደሮች የሥራ ክንውን ሪፖርት በየጊዜው እንዲያቀርቡ ያደርጋል።

## ምዕራፍ አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 9. የቀበሌ መስተዳደሮች ማዘጋጃ ቤቱን በተመለከተ ስለሚኖራቸው ግዴታና ኃላፊነት

ቀበሌዎች ከማዘጋጃ ቤቱ የሚሰጡ መመሪያዎች፤ ለሥራ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የመስጠትና የመቀበል ግዴታ አለባቸው

### 10. ተፈጻሚነት

ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፤ ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተመለከቱት ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም።

### 11. ዝርዝር ደንብ የማውጣት ሥልጣን

ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም እንደአስፈላጊነቱ ማዘጋጃ ቤቱ ዝርዝር የአፈጻጸም ደንብና መመሪያ በማመንጨት በሥራና ከተማ ልማት ቢሮ በኩል ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ

ያቀርባል፣ ሲጸድቅም በሥራ ላይ ያውላል፤

12/ <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ይህ አዋጅ በሥራ ላይ እንዲውል የክልሉ መንግሥት አስፈጻሚ አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

13/ <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ሐረር ሐምሌ 27 ቀን 1990 ዓ.ም

አብዱላሂ ኢድሪስ

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ

መንግሥት ፕሬዝዳንት